የአማራ አቅም ግንባታ ተቋም
የጀግኖች ማህደር

# ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ




ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ በኢትዮጵያ የሕክምና ታሪክ፣ በከፍተኛ ትምህርት እና በሕዝባዊ አገልግሎት የማይረሳ አሻራ ያኖሩ ታላቅ ምሁር እና የሕዝብ መሪ ናቸው። ከሕክምና ሙያቸው ጀምሮ እስከ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸው ድረስ ያሳዩት ቁርጠኝነት፣ ጀግንነት ምንጊዜም አይረሳም።
አሥራት ወልደየስ ከአቶ ወልደየስ አልታዬና ከወይዘሮ በሰልፍይዋሉ ፅጌ በሰኔ 12 ቀን 1920 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተወለዱ። ገና በሕፃንነታቸው ወላጆቻቸው ከተለያዩ በኋላ ከእናታቸው ጋር ወደ ድሬዳዋ በማቅናት ዕድገታቸውን በዚያ አሳለፉ። በድሬዳዋ በቄስ ትምህርት ቤት ከየኔታ ለማ ወልደመስቀል ዘንድ ተምረው የድቁና ማዕረግ ተቀበሉ። ይህ የአብነት ትምህርት ለሕይወታቸው መሠረት በመሆን በሥነ-ምግባር፣ በትህትናና በጥልቅ አስተሳሰብ እንዲታወቁ አድርጓቸዋል።
ከዚያ በኋላ በአዲስ አበባ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተምረው ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ወደ ግብፅ ተልከው በቪክቶሪያ ኮሌጅ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። በመቀጠልም በስኮትላንድ የሚገኘው ታዋቂው የኤድንበራ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት በ1946 ዓ.ም. በብቃት አጠናቀው ተመረቁ። በውጭ ሀገር ተምረው የተመለሱ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን የቀዶ ሕክምና ስፔሻሊስቶች መካከል አንዱ ሆኑ።

ከትምህርታቸው በኋላ ከፍተኛ የመንግሥት ሹመት ቢቀርብላቸውም፣ ሥልጣንን ሳይመርጡ በሕክምና ሙያቸው ሕዝባቸውን ማገልገልን መረጡ። ሀብታምም ሆነ ደሃ፣ ከፍተኛ ባለሥልጣንም ሆነ ተራ ገበሬ፣ ሁሉንም በእኩል ክብርና በተመሳሳይ ትኩረት በማከም የሕዝብ ፍቅርና አክብሮት አተረፉ።

በሕክምና ዘርፍ ያበረከቱት አስተዋፅኦ እጅግ የላቀ ነው። ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልን በማቋቋም፣ የሕክምና ትምህርትን በማስፋፋት፣ በርካታ ሐኪሞችን በማሰልጠንና ተቋሙን በመምራት በኢትዮጵያ የሕክምና ታሪክ የማይረሳ አሻራ አኑረዋል።

በ1990ዎቹ መጀመሪያ የፖለቲካ ለውጥ በኢትዮጵያ ሲከሰት፣ ፕሮፌሰር አሥራት የሕዝብ ጉዳዮች በበለጠ ትኩረት ሊያስፈልጉ እንደሚገባ በማመን ወደ ፖለቲካ ገቡ። በሽግግር ጉባኤው ላይ ያቀረቡት "ሀገር ለማስገንጠል ውክልና ተሰጥቶኝ አልመጣሁም" የሚለው ንግግር እስከዛሬ ድረስ በሰፊው ይጠቀሳል።

በ1984 ዓ.ም. መዐሕድን ከመሰረቱት መካከል በመሆን የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆነው አገልግለዋል። በዚህ ዘመን የፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት ከፍተኛ ተግዳሮቶች ገጥመዋቸው፤ ተደጋጋሚ የስም ማጥፋት ዘመቻዎች፣ እስራት እና የፍርድ ሂደቶችን ተቋቁመዋል።

በእስር ቤት ቆይታቸው ወቅት የልብ ሕመማቸው ተባብሶ ቢታመሙም፣ የሕክምና አገልግሎት በወቅቱ በቂ እንዳልነበረ ተነግሯል። በኋላ ወደ አሜሪካ ሄደው ሕክምና ቢጀምሩም በ1991 ዓ.ም. በፔንሲልቬንያ ሆስፒታል ሕይወታቸው አለፈ። ህልፈታቸው በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ የዜና ተቋማት ሰፊ ሽፋን አግኝቶ ነበር።
ዛሬ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ እንደ የሕክምና ባለሙያ፣ እንደ አስተማሪ፣ እንደ ተቋም ገንቢ እና እንደ ሕዝባዊ መሪ ይዘከራሉ። በሙያቸው ያሳዩት ትህትና፣ በሕዝብ አገልግሎት ያሳዩት ቁርጠኝነት፣ በእምነታቸው ላይ ያሳዩት ጽናትና ለኢትዮጵያ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ለትውልድ የሚተላለፍ የታሪክ አሻራ ሆኖ ቀጥሏል።

# ጎቤ መልኬ (ዋዋ)



ጎቤ መልኬ (ዋዋ) ከአባቱ መልኬ ተገኝ እና ከእናቱ ይሳለሙ ደምለው ጥቅምት 20 ቀን 1958 ዓ.ም. በጎንደር ክፍለ ሀገር፣ ወገራ አውራጃ፣ በጠገዴ ወረዳ አዴት ቀበሌ በአመራ ጎጥ ተወለደ።
ጎቤ ከተከበረና ባለፀጋ ቤተሰብ የተገኘ ቢሆንም፣ ሀብቱን ለራሱ ሳይሆን ለህዝብ ጥቅም የሚያውል ቅን እና ለጋስ ሰው ነበር። ለተወለደበት አካባቢ እስከ 48 ኪሎ ሜትር የሚደርስ መንገድ በማሰራት ለህዝብ አገልግሎት አበርክቷል፤ በዚህ ሥራውም የመሀንዲስ ማዕረግ አግኝቷል።

በ2007 ዓ.ም. በወልቃይትና ጠገዴ የወሰንና የማንነት ጥያቄ ዙሪያ የተነሳውን ትግል ተከትሎ ሀምሌ 5 ቀን ወደ ትጥቅ ትግል ተቀላቀለ። የጠገዴን መሬትና የአካባቢውን ህዝብ ለመከላከል በግንባር ቀደም ከተሰለፉ ታጋዮች መካከል አንዱ ነበር።

በትግል ዘመኑ በዓይን ህመም ሲሰቃይ ቢቆይም፣ በ2008 ዓ.ም. በጎንደር ሆስፒታል ተኝቶ ሳለ ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ መከበባቸውን ሲሰማ ህክምናውን ትቶ ወደ ግንባር በመሄድ ከታጋዮች ጎን ተሰልፎ ተዋግቷል። ይህም ለወገኑ የነበረውን ቁርጠኝነትና መስዋዕትነት ያሳያል። በአንድ ቃለ ምልልስም “እኛ ንፁህ አማራ ነን” በማለት የማንነት አቋሙን ገልጿል።

ጎቤ መልኬ በ2009 ዓ.ም በ51 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። በጎቤ የተሰሩ መንገዶች ላይ “ጎ” የሚል ፊደል በመጻፍ መታሰቢያው እንዲኖር ተደርጓል።

ጎቤ መልኬ ሕይወቱን፣ ጉልበቱንና ሀብቱን ለህዝቡ ያሳለፈ ሰው ነበር። በህዝብ አገልግሎት፣ በመስዋዕትነት እና በወገን ፍቅር የተመሰከረው ታሪኩ ለመጪው ትውልድ የጀግንነት፣ የመስዋዕትነት እና የሕዝብ አገልግሎት አርአያ ሆኖ ይኖራል።

# ሻለቃ (ሜጀር ጀነራል) ውባንተ አባተ



ሻለቃ (ሜጀር ጀነራል) ውባንተ አባተ የተወለዱትና ያደጉት በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን ልዩ ስሙ እስቴ (ጀግና አምባ/ጉና) በተባለው አካባቢ ነው። በትግል ስሙ "ሜጀር ጀነራል" የሚጠራው ሻለቃ ውባንተ አባተ፣ ቀደም ሲል በፌደራል ፖሊስ ሠራዊት ውስጥ በከፍተኛ የአመራርነት ደረጃ አገልግሏል። ከፖሊስ ሠራዊት ከወጡ በኋላ በጎንደርና አካባቢው ስኬታማ የነበሩ የግል ነጋዴና ባለሀብት ነበር። በአማራ ሕዝብ ላይ የተደቀነውን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ በሚል የያዙትን ስኬታማ የንግድና የቤተሰብ ሕይወት በመተው ወደ በረሃ በመውረድ የፋኖን ትግል ተቀላቀለ። በደቡብ ጎንደር የታዋቂውን የ"ጉና ብርጌድ" መስራችና መሪ ነበር።

አገር ሰሪዉ ታላቁና ጀግናው የአማራ ሕዝብ በ21ኛዉ ክፍለ ዘመን እንደሕዝብ እንዴጠፋ ሲወሰንበት ሞቱን ቁጭብለን አናይም ብለዉ ነፍጥ አንግበዉ አገዛዙን ፊት ለፊት ከተጋፈጡት ሀያሌ ጀግኖች መካከል ዉቤ ግባር ቀደሙ ነበር። አማራነትን በሞታቸዉ እያፀኑ ከሚገኙ ሀያሌ ጀግኖች መካከል ሜጄር ጀኔራል ዉባተ አባተ እናታናሹ አሌክስ አባተ ግባር ቀደም የአማራ የቁርጥ ቀን ልጆች ናቸዉ። በ2002የፌደራል ፖሊስ አባል እያለ በአማራ ተወላጆች ላይ የሚደርሰዉን በደል ፊት ለፊት በመድረክ በመጋፈጥ የጠላት ህዋት አመራሮች ሲያሳድዱት አንዱን የህዋት አመራር በመግደል ከሱማሌ ጅጅጋ ቀብርዲሀር በመነሳት ወደ መናገሸዋ ጎንደር ከተማ የመጣ ሲሆን በሌለበት ተከሶ 25 አመት ጽኑ እስራት ተፈርዶበት ነበር።

ከዚያ ቀደም ብሎ በአንዳድ አደረጃጀቶች የተሳተፈ ቢሆንም በ2008 ኢ.ም ሀምሌ አምስት ኮ. ል ደመቀ ዘዉዱ ሲታፈን ፊት ለፊት ከተፋለሙ ጀግኖች መካከል ዉባንተ አባተ አንዱ ነበር።

በ2008 ጎንደር ለአለም ድምጿን በአሰማችበት ሰላማዊ ሰልፍ ግንባር ቀደም ተዋናኝ ነበር። ከዚያ በኋላ በሚደረጉ የቤት ዉስጥ የመንገድ መዝጋት አድማዎች ላይ የዉባንተ ድርሻ ከፍተኛ ነበር። በ2009 ህዋትን ለመፋለም ጫካ ከገቡ አርበኞች ጋር በመገናኘት በሀሰብ በፋይናስ ድጋፍ ያደርግም ነበር። በተለይ ቁስለኞችን በማሳከም ጉልህ ሚና ነበረዉ። በአጠቃላይ ህዋህትን ከስልጣን ለማዉረድ እና በአማራ ህዝብ የሚደርሰዉን ግፍ ለማስቆ በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ዉቤ ከፊት አለ። ከወልቃይት እና ከራያ የወሰን አስመላሽ ኮሚቴዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው። በአማራ ላይ የሚደርሰዉን ግፍ ለመከላከል ለመቀልበስ ወጥ አደረጃጀት የግድ በመሆኑ የአባቶቹን ክብር ለመመለስ ፋኖ በጎንደር ከተማ ሲደራጅ በስራ አስፈጻሚዉ ዉስጥ በመግባት ፋኖን አደራጅቷል መርቷል። በ2012 ጎንደር አየር ማረፊያ አዘዞ ተክለሀይማኖት እርሱ የሚመረዉ ጠንካራ ግዙፍ ሻለቃ መስርቶ ችግር በተፈጠረበት ሁሉ ጡሩን እየመራ ከፊት ይገኝ ነበር። በ2012 የአማራ መደራጀትን ከሚያምኑ አያሌ ጀግኖች መካከል ግንባር ቀደም በመሆን በሃሳብና በፋይናንስም ያግዝ ነበር። በ2013 ህዋህት የሰሜን እዝን ስትወጋ ከንጋቱ 10 ሰአት ጎንደር ተነስቶ በግል መኪናዉ ሁመራ ማይካድራ ጦርነት ወደተከፈተበት የአማራ ህዝብ ያመራ ግባር ቀደም ጀግና ነበር።

በ2013 ህዋህት የሰሚን እዝን ሲወጋ ሜጀር ጄኔራል ዉባንተ አባተ ከንጋቱ 10 ሰአት ላይ በግል መኪናዉ ወደ ሴቲት ሁመራ ዞን ህዋህት ጦርነት ወደ ከፈተበት ማይካድራ በመድረስ ፊት ለፊት ተዋግቷል አዋግቷል። ተከትለዉት ከኋለዉ የደረሱትን ታነሹን አሌክስን እና ፀገናዉ አለማየዉን የአካባቤዉ ጀግኖች የአማራ ልዩ ሀይልን በማቀናጀት በሁመራ ዞን በሶስቱ የጠለምት ወረዳዎች በመንቀሳቀስ ጠላትን ተፋልሟል በህዋህት ተከቦ የነበረዉን ጀኔራል ሙሉአለም ታደሰን ከበባዉን በመስበር ካወጡት የአማራ ጀግኖች መካከል ዉቤ አንዱ ነበር።

ዉባንተ ሀምሌ 16 ቀን2013 አዲርቃይ ላይበተደረገው ዉጊያ ጠላት ከፍተኛ ማጥቃት ሲያደርግ ፋኖ ሀብቴ ኪዴ እና ፋኖ አዳነ ጎሹ ሲሰዉ ከበባ ዉስጥ የገቡትን 16 የፋኖ አባላትን ከሀብቴ ወልዴ ጋር ተፋልሞ አትርፏቸዋል።
በሰሜኑ ግንባር ከብዙ እልህ አስጨራሽ ዉጊያ በኋላ ህዋሀት የወረራ አቅጣጫዉን በመቀየር በራያ ቆቦ ሲያደርግ የጎንደር ፋኖ ከደባርቅ ደብረታቦር ጋይት ደብረዘቢጥ በማድረግ ሀምሌ 28ቀን 2013 ዓ ም በደብረዘቢጥ የጎንደር ፈርጦች ጀግንነታቸዉን ለአለም ያሳዩበት የህዋሀት አይነኬ ምሽግ የተሰበረበት የቴዎድሮስ እና የገብርየ ልጆች መሆናቸው የተመሰከረበት ጀብድ ሲፈፀም የውባንተ አዋጌነት ተዋጊነት ጎልቶ የታየበት ነበር። በሐምሌ 30 /2013 ከባድ ትንቅንቅ ሲደረግዉሎ ከቀኑ ዘጠኝ ፣ሰአት ላይ ከበባ ውስጥ የገቡትን ደረጀ በላይ እና አርበኛ አይሸሽም ጨቅሌን ለማዉጣት ገብቶ እነርሱን ካወጣ በኋላ ከጠላት በተተኮሰ የስናይበርጥይት ተመቶ ከባድ ቁስለኛ ሁኖ በጋይት እና ደብረታቦር ሆስቢታል ህክምና ላይ እያለ ህክምና አቋርጦ ወደግንባር በመሄድ ጠላትን ተዋግቷል አዋግቷል።
ከህመሙ ሳያገግም በደብረዘቢጥ ፣በጋይንት ፣ ጎብጎብ ፣ ሳአሌ፣ ጥጥራ ፣ጉና ፣ወለላ ባህር ፣ክምር ድንጋይ ፣ጋሣይ ከጠላት ጋር የተዋጋባቸዉና ያዋጋባቸዉ ቦታዎች ናቸው። ህዋሀት ወደ አዲስ አበባ የሚያደርገውን ጉዞ የከሸፈበትእና ወሳኝ ቦታ ብሎ ለመያዝ ብዙ ዋጋ የከፈለበት ደብረታቦር የመያዝ እቅድ ሲከሽፍበት ሁሉም ትቶ ሲሸሽ ወንድሞቹን አሌክስን ታላቁን ነጋን በመያዝ ከመከላከያ ጋር ሁኖ በመፋለም ህዋሀት ጋሣይ ላይ ተመቶ ሲመለስ የውቤ እና የወንድሞቹ ሚና ከፍተኛ ነበር። ለመደራጀት ትልቅ ቦታ የሚሰጠዉ ውባንተ አባተ በገብርየ ምድር ጋይት ግንባር ላይ ገብርየ ሻለቃን መሠረተ።ከአንድ ወር እረፍት በኋላ ጦርነቱ ሲቀጥል ነሀሴ 26 2013 ዓ ም ዘጠኝ የህዋሀት አባላት በቆረጣ በመግባት የመከላከያን መካናይዝድ ሊይማርኩ ሲሉ ብቻውን ተጋፍጦ በመደምሰሱ በመከላከያ ሰራዊት ዘንድ የዘመናችን ገብርየ የሚል አድናቆትን አግኝቷል። ለገብርየ ሻለቃ ሽልማት ያበቀውም እሱ ነው። ነሀሴ 27 ቀን ከጠላት በተተኮሰ የዙ23 ጥይት ፍንጣሪ በድጋሚ ቆሰለ።ጦርነቱም ለሁለት ወር ያክል ቆሞ ስለነበር ጥይቱ ባይወጣም በቂ ህክምና አግኝቶ ተመለሰ።
ሀምሌ 19,2015 ዓ ም እምነት ደፋሪዉ አገር አፍራሹ አብይ አህመድ በተከበረዉ ደብረሲና ገዳም አመታዊ ክብረባል በሮብ ቀን እርድ በመታረዱ ለምን በሚል በተከፈተ ጦርነት ለእነ አርበኛ ደረጀ በላይ ገብርየ ሻለቃን እና የጎንደርን ፋኖ መርቶ በመድረስ ታሪክ ፈጽሟል። ሀምሌ 24 በደብረታቦር የተደረገዉን ጦርነት በስልክ አቀናጅቶ ትዛዝ እየሰጠ መርቷል። ሀምሌ 26 2015ዓ/ም ከጧቱ 5,ሰአት ላይ ወደ ባህርዳር ለጦርነት በሚጓዝ የገዘዙ ጦር ላይ መንገድ አዘግቶ እራሡ ጦርነቱን በመጀመር የጎንደርን ፋኖ አቀናጅቶ ከሀብቴ ወልዴ ጋር እየመራ ለተከታታይ ሠባት ቀን ሙሉ ጎንደርን ተቆጣጥሮ የቴዎድሮስ የገብርየ ትንፋሽ መሆኑን አስመስክሮበታል። ነሀሴ 4,2015 ዓ ም ግራኝ በር ላይ በተደረገ ጦርነት ከጠላት ጋር የእጅ በእጅ ዉጌያ ያደረገ ሲሆን በዚህ ዉጊያ ጥይት መሙላት ያልተቻለበት ቦንብ እንደ ድንጋይ የተወረወረበት ዉባንተ ፣አሌክስ ፣አበበ፣ተመስገን ጀብድ የፈፀሙበት ጊዜ ነው። ዉቤ ግራኝ በር ሲነሳ ልዩ ስሚት ይሰመው ነበር። ከጦርነት ጎን ለጎን በአማራ ክልል የመጀመሪያ የሆነውን ጉና ክፍለጦር መሰረተ። መስከረም 13,2016 ዓ ም ከመና መቀጠዋ ጎንደር አምስት ቀን ገብርየ ሻለቃን መርቶ በመግባት ከ እነ ሀብቴ ፣ከእነሰለሞን ፣ናሁሰናይ ጋር ጎንደርን በመቆጣጠር አገዛዙን እራቁቱን ያስቀረ ኦፕሬሽን ሰርቷዋል። የጉናዉ ነብር የጎንደሩ የአማራው ፈርጥ ዉባንተ አባተ በሰላ አንደበቱ ደጉን የአማራ ገበሬ በጀርባዉ አራት ጥይት ተሸክሞ 50 የሰሜን በየምድር ወረዳዎች በመንቀሳቀስ አሰልጥኗዋል ፍትህ አስፍኗል። በአጠቃላይ በዚህ ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ላይ የአምደ ፅዮንን ጦር የመዘዙ የአማራ ሙሴዎች ጠላቶቹን በማንበርክ የአማራን የቀደመ ልዕልናዉ ለማሥመለሥ ከፊት ከተሰለፋት አንዱ የሆነዉ ዉባንተ አባተ ባለፋት ዘጠኝ ወራት ብቻ ከ172 በላይ አዉደዉጌያዎችን በታላቅ ብቃት እና ጀብዱ የመራ ሲሆን 128ቱን በአካል እየተዋጋ ያዋጋቸዉ ትልልቅ ምሽጎችን በመስበር ጀብድ ፈፅሞባቸዋል። ቀሪ 44ቱን ዉጌያዎች ከዋና ማዘዣ ኮማንድ ቦታ በመሆን በስትራቴጃዊ የጦር ጥበብ ወታደራዊ ስምሪት በመሥጠት የጠላትን አከርካሪ እንደሰበረ የሜጄር ጀኔራል ዉባንተ አባተ የጦር ሜዳ ዉሎ ያስረዳል። የአማራነት አዕምዶች ጎንደር፣ሸዋ፣ ጎጃም፣ወሎ አንድነታቸዉን በከበረ መስዋዕትነታቸዉ እንዲያደምቁ የአንድነት ኪዳናቸዉን በትግላቸዉ እንዲያፀኑ ሞዴል ሁኖ የወጣ የዘመናችን ክስተት መሪ ነበር። ለአማራ ህዝብ ፍታህዊ የህልዉና ትግል እንደ ሻማ ቀልጦ እራሱን መስዋት አድርጎ ትግሉን ወደ ላቀ ደረጃ ያሻገረ አይተኬ የአማራ ልጅ ነዉ።
በአጠቃላይ የዉባንተ ብርታት የመኖሩ ሚስጥር የሆነዉ ጠባቂየዉ ማያ መነፀሩ ሻለቃ አሌክስ አባተ ጥቅምት 16,2016 ዓ ም እስቴ ከተማ ከጠላት ጋር ተፋልሞ ጠላትን እረፍርፎ በብዙ ሰዎች አደራ የተሰጠዉን ወንድሙን ትቶት ተሰዉቷል።

# የብርጋዴል ጀኔራል አሳምነው ፅጌ



ብ/ጀኔራል አሳምነው ፅጌ ከመጋቢ ጥበባት ፅጌ ተበጀ ከእናታቸው ከወ/ሮ ውብ ሰፈር አሳየ በ1951 ዓ.ም በድሮው የላስታ አውራጃ በአሁኑ ቡግና ወረዳ ጉድባ በታች ልዩ በታው ቆብ ተክለ ሀይማኖት ተወለዱ። ብ/ጀኔራል አሳምነው ፅጌ እድሚያቸው ለትምህርት እንደደረሰ የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቅዱስ ላሊበላ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ት ቤት አጠናቀዋል። ብ/ጀኔራል አሳምነው ከሁሉ በፊት ሳይማር ያስተማረውን ወገናቸውን ለማስተማር ፅኑ እምነትና ፍላጎት ስለነበራቸው ለመምህርነት የሚያበቃቸውን ስልጠና በደሴ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ተከታትለዋል።ከዚህም ቡኋላ ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ በቀድሞው የየጁ አውራጃ ስሪንቃና ጋላ ጊዮርጊስ ት/ት ቤቶች ለሁለት አመታት አስተምረዋል።በመቀጠልም ወደ መቄት ሀና መኳት ት/ት ቤት ተዛውረው በመምህርነት ሙያ አገልግለዋል።
ብ/ጀኔራል አሳምነው በ1981 ዓ.ም በወቅቱ የነበረውን ወታደራዊ አገዛዝ ለማስወገድ በተደረገው ህዝባዊ ትግል የኢትዮጵያን ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ድልን ተቀላቀሉ።
ትግሉን ዳር ለማድረስ በገቡት ቃል መሰረት ወታደራዊና የህክምና ሙያ ስልጠና ከወሰዱ ቡሀላ በተለያዩ አውደ ውጊያወች አኩሪ የሆነ ግዳጅ በመፈፀም ተልእኳቸውን አጠናቀዋል።በመጨረሻም የጀመሩትን ትግል በድል ለመደምደም የላቀ አስተዋፅኦ በማድረግ የድሉ ተቋዳሽ ሁነዋል።ትግሉ የሚጠይቀውን አገልግሎት #ለአራት ተከታታይ አመታት አበርክተዋል።
ብ/ጀኔራል አሳምነው ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው በመምጣት የቡግና ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ በመሆን የወረዴውን ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴወችን በብቃት በመምራት ሁለንተናዊ ለውጥና እድገት በማስመዝገብ ሀላፊነታቸውን ተወተዋል።በዚህ ወረዳ በቆዩባቸው የአራት አመታት ስራቸው በመሰረተ ልማት ትርጉም ያለው ውጤት ያስመዘገቡ በሳልና ትሁት መሪ ነበሩ።
ብ/ጀኔራል አሳምነው ቀደም ሲል ያሳዩት ያመራር ጥበብና ክህሎት መነሻ ለተሻለ ሀላፊነት ሊመጥኑ እንደሚችሉ ስለታመነበት ከ1988-1990 ዓ.ም የአማራ ክልላዊ መንግስት የስራ አመራር ኢንስቲቲዩት ሁነው ተመድበው ብቁና ንቁ የሰው ሀይል በማፍራት የስራ ሀይል ፈጥረዋል።በተለይም በየደረጃው ሊመጥን የሚችል የስራ ሀይል ማምረት የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ስለነበር ጀኔራሉ የመንግስትና የዜግነት ግዴታቸውንና ሀላፊነታቸውን በብቃትና በጥራት ተወተዋል።
ብ/ጀኔራል አሳምነው ስብእናቸው ትህትናቸው ስነምግባራቸው ሰወችን በመርዳት የሚያሳዩት ማህበራዊ ግንኙነት ወደርም ሆነ አቻ የማይገኝላቸው የግል ባህሪወቻቸው መሆናቸውን በቅርብ እምናውቅ እናረጋግጣለን።
ብ/ጀኔራል አሳምነው ለተወከሉት ህዝብ ታማኝ ላገራቸው ቀናይ በሚመደቡት ቦታ ሁሉ የሚመጥኑ ለመሆናቸው የኋላ የስራ ህይወት ታሪካቸው በቂ ማረጋገጫም ነው።
የሻቢያ መንግስት አገራችን በወረረ ጊዜ ከ1990-1993 ዓ.ም ድረስ በኔትራል_ኮሊነር ማእረግ ተሹመው ወደ ግምባር በማምራት የ22ኛ ክፍለጦር ምክትል አዛዥ በመሆን በባድሜ ገዛ_ገብረስላሴ ግምባር ብቁ አመራር በመስጠት ተዋግተዋል አዋግተዋል።

ብ/ጀኔራል አሳምነው ደፋር ቆራጥ አርበኛ ነበሩ። ይህም ልዩ ተሰጧቸው ወራሪው ሀይል ባጭር ጊዜ በመጣበት እንዲመለስ በማድረግ ድርሻቸውን በመወጣት አገራዊ ልእልናችንን እንድንጎናፀፍ አድርገዋል። ብ/ጀኔራል አሳምነው የጦር ሜዳ ውሏቸው በወኔ የታጀበና ልዩ ግምት የሚሰጣቸው ሁኖ በመገኘቱ ከ1994 ጀምረው በብርጋዴል ጀኔራል ማእረግ የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ዲን እና የአየር ሀይል የሰው ሀይል አስተዳደር ሁነው ተቋማቱን በብስለትና በብልሀት አመራር ሰተው የጦር ሜዳ ምሀንዲስም ነበሩ።

ብ/ጀኔራል አሳምነው ባሳዩት ያመራር ጥበብ ከሌሎች መኮንኖች የላቀ ብልጫ በማሳየታቸው ለልዩና ለከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርት አሜሪካን ሀገር ሂደው እንዲማሩ እድል ተሰጥቷቸው ትምህርታቸውን ለሁለት አመታት ተከታትለው ባጥጋቢ ውጤት አጠናቀው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ራእያቸውን ለማሳካት ጥረት አድርገውም ነበር። ሆኖም በወቅቱ ከውጭ መልስ የአየር ሀይል ምክትል አዛዥና የጦር ሀይልሎች ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር በመሆን ለአጭር ጊዜም አገልግለዋል።

ይሁን እንጅ ጀኔራሉ ለህዝብ መብት መከበርና ለሀገራቸው ህልውና በፅኑ የሚታገሉ በመሆናቸው በመካከል በተፈጠረ ችግር የእድሜ ልክ ፍርድ ተወስኖባቸው ከ2001-2010 ዓ.ም ለ9 አመታት ያክል በእስር እንዲቆዩ ተደረጉ።

ጀኔራሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ትግልና በይቅርታ በመንግስት እንዲፈቱም ተደርጓል። ብ/ጀኔራል አሳምነው አገርና ህዝብን ለማገልገል አቅም ማሳደግ ብቸኛው መንገድ መሆኑን በመረዳት በማኔጅመንት የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በቢዝነስ አድምንስትሬሽን ሁለተኛ ድግሪያቸውን ሰርተዋል።የህዝብ አስተዳደርና የፖለቲካ ሊቅም ነበሩ።

ከእስር እንደተፈቱ ሀገራዊ ለውጡን ለማስቀጠል እውቀታቸውንና ልምዳቸውን በመጠቀም አገራቸውን ለማገልገል ካላቸው ፍላጎት የተነሳ የአማራ ክልል መንግስት የሰላምና ደህንነት ቢሮ ሀላፊ እንዲሆኑ በተሰጣቸው ሹመት ሀላፊነታቸውን በመወጣት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሌት ከቀን እየደከሙ እየሰሩ እያሉ በውል ባልታወቀ ምክንያት ሰኔ 17/2011 ዓ.ም በተወለዱ በ60 አመታቸው ህይወታቸው አልፏል።

እንቁና ሀገር ወዳድ የሆኑት ብ/ጀኔራል አሳምነው ያላማ ፅናት ያላቸው ሩህሩህ የህዝብና የሀገር ፍቅር ያላቸው እንዲሁም የጀመሩትን የመጨረስ ፅኑ እምነት የነበራቸው ልበ ሙሉ እና ጠንካራ ነበሩ።

ወንድማችን ያገር ኩራት ነበሩ ዛሬ ግን አጣናቸው። ክልላችን ብሎም ሀገራችን ዛሬ አንድ ትልቅ ሰው አጣች ያሳዝናል። ወንድማችን ብ/ጀኔራል አሳምነው የ3 ወንድ ልጆችና የአንድ ሴት ልጆች አባት ነበሩ።

ሆኖም ለሰው ልጅ ሞት የማይቀር ነባራዊ ሁኔታ ነውና እግዚአብሄር ነብሳቸውን በአፀደ ገነት ያኑርልን።


ብርቅየና እንቋችን ብ/ጀኔራል አሳምነው የምንመካባቸውና የምንኮራባቸው ወንድማችን በማጣታችን ልባችን ተሰብሯል ህሊናችን ቆስሏል።ስለሆነም ፣ወላጆች፣ወንድሞች፣እህቶች፣ባ

ለቤታቸው ፣ልጆቻቸው እንዲሁም ቤተሰቦችና ሌሎች የቅርብ ጓደኞችና በአጠቃላይ ለክልላችንና ብሎም ለሀገራችን ህዝቦች በሙሉ እግዚአብሄር መፅናናትን ይስጥልን።

በአጠቃላይ ምርጥና እንቁ የሆኑትን ብ/ጀኔራል አሳምነው ፅጌ ማመን በሚያዳግት መንገድ እንደ ቀላል በሞት በመለየታቸው የተሰማን ሀዘን መሪር ቢሆንም ሺ አሳምነወች ስለተወለድን የጀመሩትን ትግል ከዳር እናደርሳለን። እግዚአብሄር ነብሳቸውን በአፀደ ገነት ያኑርልን አሜን::

ምንጭ ከቀብር አስፈፃሚ ኮሚቴው

# ጋዜጠኛ፣ደራሲና ወታደራዊ መሪ ኮማንደር አሰግድ መኮንን



- **የአርበኛው ሙሉ ስም፡-** ጋዜጠኛ፣ ደራሲና ወታደራዊ መሪ ኮማንደር አሰግድ መኮንን እንግዳወርቅ
- **የእናት ስም፡-** ወይዘሮ ዘርጊ በየነ
- **የሕይወት ዘመን፡-** ሰኔ 12 ቀን 1958 ዓ.ም. (June 19, 1966 G.C.) ተወለደ።
- **የትውልድ ቦታ፡-** ሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ በይፋትና ጥሙጋ አውራጃ፣ በኤፍራታና ግድም ወረዳ፣ ልዩ ስሟ "እያሪኮ" በምትባል ታሪካዊ መንደር።

**የሕይወት ፍልስፍና እና ቁልፍ ጥቅሶች**

**"ሆዳም ትውልድ ሀገርም ታሪክ የለውም"**

**"አማራ የሚያሸንፈው አማራ ነኝ ብሎ በማንነቱ ሲደራጅ ብቻ ነው"** ኮማንደር አሰግድ በድርሰናቱና በመጻሕፍቱ ለትውልድ ያስተላለፈው ይህ የታሪክ መመርያ የአማራ ሕዝብ ራሱን ከህልውና አደጋ ለመከላከልና ጥቅሙን ለማስከበር ሊከተለው የሚገባው ብቸኛው የማሸነፊያ ቁልፍ መሆኑን በፅኑ ያምንበት ነበር።

**አጭር ማጠቃለያ**

ኮማንደር አሰግድ መኮንን በሀገራዊና በብሔረሰባዊ የፖለቲካ ንቅናቄ ውስጥ ጉልህና የማይፋቅ አሻራ ያሳረፈ ታላቅ የዘመናችን ቁንጮ አርበኛ ነው። በቀድሞው የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ) ውስጥ በጽሕፈት ቤት ደረጃ ለአማራ ሕዝብ መብትና ክብር መከበር በቁርጠኝነት የታገለ ሲሆን፣ በዕውቀትና በብዕር ትግሉም ከ15 በላይ ተጽዕኖ ፈጣሪና ታሪካዊ መጻሕፍትን ለንባብ አብቅቷል። ከእነዚህም መካከል፡- *ኮብላይ፣ ጥብቅ ሚስጥር፣ የቃል ፅናት፣ ነፀብራቅ፣ አዳኝ እና ገዳይ፣ ፋና ወጊዎቹ፣ የወያኔ ሴራ፣ ያላለቀው ጦርነት፣ ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ፣ ማጉረምሰቢው፣ የጥላቻ መንፈስ፣ የጠፋው ተራራ ትንሳኤ፣ ሄራ ሰኔ 15፣ ጎንደር ደርሶ መልስ* እና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው።

የአማራ ሕዝብ የሕልውና አደጋ ሲያንዣብብበት የብዕር ትግሉን ወደ ወታደራዊ መሪነት በመቀየር የታሪካዊው የፋኖ አደረጃጀት ግንባር ቀደም መስራች፣ አሰልጣኝ፣ የጦር ስትራቴጂስትና የዕዝ መሪ በመሆን እስከ መስዋዕትነት የደረሰ ተጋድሎ ፈጽሟል።

## 2. የልጅነት ዘመን እና አስተዳደግ

**የቤተሰብ ታሪክ:** አሰግድ መኮንን በሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ በታሪካዊው የይፋትና ጥሙጋ አውራጃ በኤፍራታና ግድም ወረዳ ልዩ ስሟ "እያሪኮ" በምትባል መንደር ከአባቱ ከአቶ መኮንን እንግዳወርቅና ከእናቱ ከወይዘሮ ዘርጊ በየነ ሰኔ 12 ቀን 1958 ዓ.ም. ተወለደ። አስተዳደጉም እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ገጠር ልጅ ከማኅበረሰቡ ባህል፣ ወግ፣ የሞራል እሴትና ጨዋነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነበር።

**ትምህርትና ዝግጅት፡-**

- **የቤተ-ክህነት ትምህርት፡-** ገና በልጅነቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በመግባት ከሀ-ግዕዝ እስከ ዳዊት ድረስ በመድገም የሀገሩን ጥንታዊ ታሪክ፣ ሃይማኖታዊ ስነ-ሥርዓትና ስነ-ጽሑፍ ጠንቅቆ እንዲያውቅ ጠንካራ መሰረት ጥሏል።
- **ዘመናዊ ትምህርት፡-** መደበኛ ትምህርቱን በሚገባ ካጠናቀቀ በኋላ በቀድሞው የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በመግባት በስነ-ጽሑፍ ዲፕሎማውን አግኝቷል። ይህ የጥበብ ስልጠናው በኋላ ላይ ለታላቅ ደራሲነቱ፣ ለጥልቅ ተንታኝነቱና ለዘጋቢ ጋዜጠኝነቱ ትልቅ የአእምሮ አቅም ሆኖታል።
- **ወታደራዊ ስልጠና፡-** በቀድሞው የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ውስጥ በመግባት መሰረታዊ የውትድርና ሳይንስን፣ ወታደራዊ ስልትንና ጠንካራ የዲስፕሊን ክህሎትን አትርፏል። ይህ ዕውቀቱ በኋለኛው ዘመኑ የፋኖን ሰራዊት በዘመናዊ ስልትና መዋቅር ለመገንባትና ለመምራት አስችሎታል።

## 3. ለአርበኝነት መነሳት

**የመጀመሪያው ተሳትፎ:** ኮማንደር አሰግድ ወደ መዐሕድ ከመቀላቀሉ በፊት በወቅቱ በባሌ ክፍለ ሀገር ይንቀሳቀሱ ከነበሩና በአማራ ሕዝብ ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት ለመከላከል ቀድመው ወደ ጫካ ከገቡት ኃይሎች ጋር በመሆን ከአሩሲ እስከ ባሌ ክፍለ ሀገር እየተዘዋወረ ይደርሱ የነበሩትን እልቂቶችና ግፎች በግንባር መክቷል። በኋላም በመዐሕድ ውስጥ በነበረው የአገልግሎት ዘመን፣ የአማራ ሕዝብ የገጠመውን ሁሉን አቀፍ መዋቅራዊ ስጋትና የተደቀነበትን የህልውና አደጋ በቅጡ ተረድቶታል።

ይህንን ስጋት በብዕሩ በመከተብ ለዓመታት ሲታገልና ትውልዱን ሲያስተምር የቆየ ቢሆንም፣ የሕዝቡ መሰረታዊ የደህንነትና የመብት ጥያቄዎች በሰላማዊ መንገድ ሊመለሱ ባለመቻላቸው በተግባራዊ ትግል ለመሰማራት ወሰነ። በተለይም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በይፋት ቀጠና (በኤፍራታና ግድም፣ በአጣዬ ከተማ ቃጠሎ፣ በቀወት፣ በገምዛና በአንፆኪያ ወረዳዎች፣ በወለጋ ቢዛሞ፣ በጎጃም መተከል እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ይደርሱ የነበሩትን ማንነት ተኮር ጥቃቶች፣ ጭፍጨፋዎችና መፈናቀሎች በተግባር ሲመለከት የትጥቅ ትግሉ አማራጭ የሌለው መሆኑን አመነ። በዚህም የአዲሱን ትውልድ የህልውና ጥያቄ ከመዐሕድ ታሪካዊ መነሻ ጋር በማስተሳሰር የፋኖን አደረጃጀት በግንባር ቀደምትነት መሰረተ።

**በፋኖ አደረጃጀት ውስጥ የነበረው ሚና፡-**

- **የይፋት ፋኖ በቀወት፡-** በመጀመሪያ በቀወት ወረዳ ይንቀሳቀስ የነበረውን "የይፋት ፋኖ" የአደረጃጀት መዋቅር በወታደራዊ ክህሎትና በፖለቲካዊ አቅም አሰልጥኖ፣ እነአርበኛ ሞላ ደስዬ በተገኙበት መድረክ ላይ በታላቅ ደምቀት አስመርቆ ተቋማዊ ቅርፅ እንዲይዝ አድርጓል። ሰራዊቱ በፖለቲካ የበሰለና የሚታገልለትን ዓላማ በግልጽ የሚያውቅ እንዲሆን አድርጓል። በ2013 ዓ.ም የህልውና ዘመቻ ሲታወጅም ከአደራጀው ፋኖ ጋር በመሆን በይፋት ግንባር (ራሳ አካባቢ) የህውኃትን ኃይል በመመከት እስከ ራያ ግንባር ድረስ ትግሉን በበላይነት መርቷል።

- **የፕሮፌሰር አስራት ብርጌድ እና አፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር ምስረታ፡-** በቀወት የነበረውን የፋኖ አደረጃጀት ካጠናከረ በኋላ ወደ ትውልድ ቀዬው ማጀቴ ያመራው ኮማንደሩ፣ "የይፋት ፋኖ በማጀቴ" የሚለውን ኃይል በፖለቲካና በጦር ሳይንስ አሰልጥኖ አስመረቀ። ይህንን ኃይል በስድስት ሻለቃዎች በማዋቀር **"ፕሮፌሰር አስራት ብርጌድ"** ብሎ ሰየመው።

በመቀጠልም በግሼ ራቤል በነአርበኛ አሸናፊ ምንዳ እና አርበኛ አበበ ጥላሁን ተደራጅቶ ይንቀሳቀስ የነበረውን የፋኖ ሰራዊት በመንዝ ጌራ ወዟድ አካባቢ ይንቀሳቀስ ከነበረው "እለይ ሻለቃ" ጋር በማዋሃድ **"ብሩኬ ደምሴ ብርጌድ"** (የቃል ፅናት በሚል መጽሐፉ የፃፈለትን ጀግናው አርበኛ ብሩኬ ደምሴን ለመዘከር) ብሎ ሰየመው። እነዚህን ሁለት ተንቀሳቃሽ የፋኖ ብርጌዶች ከሌሎች ሦስት የአባት አርበኛ አደረጃጀቶች ጋር በማጣመር፣ በታሪካዊቷ ግሼ ራቤል ምድር የመጀመሪያውን የፋኖ ክፍለ ጦር አደረጃጀት አፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር በማለት መሰረተ። አፄ ይኩኖ ዓምላክ ለአስር ትውልድ ገደማ በስደት የነበረውን ሰለሞናዊ ስርዎ መንግስት ወደ ግንዱ የመለሱበትና የንግስና ቆባቸውን የደፉባት ስፍራ ግሼ ራቤል በመሆኗ፣ ለታሪክ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው አሰግድ መኮንን ይህንን ታሪካዊ ቁርኝት በመፍጠር ክፍለ ጦሩን **"አፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር"** በማለት ሰየመው።

- **የአማራ ፋኖ ነፃ ሕዝብ ንቅናቄ እና የሸዋ ዕዝ ምስረታ፡-** በከሰም ቀጠና በተበታተነ መልኩ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የፋኖ አደረጃጀቶችን ወደ አንድ ለማምጣት ሁለት የፋኖ ተወካዮችን (ከሀገረ ማርያም አርበኛ ንጋቱ ይታፈሩን እና ከምንጃር በድሮን ጥቃት የተሰዋውን አርበኛ በኃይሉ ሙሉጌታን) ማጀቴ ከተማ ድረስ በመጥራት አወያየ። በዚህም በአንድ ወታደራዊ መዋቅር ስር በማምጣት "ከሰም ክፍለ ጦር" የተሰኘውን አደረጃጀት መሰረተ። እነዚህን ሁለት ግዙፍ ክፍለ ጦሮች (አፄ ይኩኖ ዓምላክ እና ከሰም) በማጣመር **"የአማራ ፋኖ ነፃ ሕዝብ ንቅናቄ"** የሚል ወጥ የፋኖ ሰራዊት አደረጃጀት ፈጠረ።

ይህ ንቅናቄ የራሱ የትግል ማኒፌስቶና ፍኖተ ካርታ የነበረው ሲሆን፣ ውሎ አድሮም በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ይንቀሳቀሱ ከነበሩ ከሌሎች ሁለት የፋኖ አደረጃጀቶች (የአንድ አማራ ፋኖ እና የፋኖ ምክር ቤት) ጋር በመቀናጀት ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም **"የአማራ ፋኖ ሸዋ ዕዝን"** መሰረተ። የፋኖ ኃይል ድርጅታዊ ቅርፅ፣ ወጥ ዕዝ ሰንሰለት ያለው ተቋም እንዲሆን ኮማንደሩ የአንበሳውን ድርሻ መወጣቱን የወቅቱ የዕዙ ምክትል መሪ የነበረውና የአሁኑ የአፋብን ሸዋ ጠቅላይ ግዛት አሳምነው ዕዝ ዋና ሰብሳቢ አርበኛ ኢ/ር ደሳለኝ ሲያስብሸዋ ይመሰክራል። ኮማንደር አሰግድም የዚህ ታላቅ የሸዋ ዕዝ ዋና መሪ በመሆን እስከ ሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በቁርጠኝነት፣ በታማኝነትና በአማራዊ የሞራል ልዕልና መርቷል።

### 4. ዋና ዋና አውደ ውጊያዎች፣ ገድሎች እና የጦር ስልቶች

### የተሳተፈባቸው ወታደራዊ ዘመቻዎች

- **የአጣዬ ከተማን ከቃጠሎ የማዳን ዘመቻ (ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም.)፡-** ኮማንደር አሰግድ "የይፋት ፋኖ በማጀቴን" በግንባር ቀደምትነት እየመራ፣ የአጣዬ ከተማን ሙሉ በሙሉ ለማውደም በኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በኩል የመጣውንና ተደጋጋሚ ውድመት ያደርስ የነበረውን ጽንፈኛ የኦነግ ሸኔ ቡድን ፊት ለፊት ገጥሞታል። በወሰደው ፈጣን ማጥቃት የቡድኑን አከርካሪ በመስበርና ጽንፈኛው ይንቀሳቀስበት በነበረው ቀጠና ውስጥ ዘልቆ በመግባት የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ከተማዋን ከታሪካዊ ጥፋት ታድጓታል።
- **የዲዶ ምሽግ ስባሪ እና የልዩ ኃይል ማዳን ዘመቻ (ጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም.)፡-** እጅግ አስቸጋሪና ስልታዊ የነበረውን የጠላት "የዲዶ ምሽግ" በመስበር፣ በተቀነባበረ የውስጥ ሴራ ተከቦ ሙሉ በሙሉ ሊደመሰስ የነበረውን ከ300 በላይ የሚሆነውን የአማራ ልዩ ኃይል አባላትን የታደገበት ታላቅ ጀብዱ ነው። ኮማንደሩ ጨፋሮቢት ከተማ ውስጥ ዘልቆ በመግባት የጠላትን ከበባ ሰብሮ የወገን ኃይል በድል እንዲወጣ በማድረግ አለኝታነቱን በተግባር አስመስክሯል።

- **የማጀቴ አባልአምባ ታሪካዊ ውጊያ (ሚያዚያ 23 ቀን 2016 ዓ.ም.)፦** በአፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር ስር የተካሄደው የመጀመሪያው ግዙፍ የማጥቃት አውደ ውጊያ ሲሆን፣ በማጀቴ ከተማ ልዩ ስሟ "አባልአምባ" በተባለች ስፍራ በአገዛዙ ዙፋን አስጠባቂ ኃይል ላይ ተፈጸመ። በዚህ እጅግ ከባድ ውጊያ የጠላት ጦር ሙሉ በሙሉ የተደመሰሰ ሲሆን፣ ከፋኖ ወገን አንድ ሰራዊት ብቻ በመሰዋቱ የክፍለ ጦሩን የውጊያ ብቃትና ዝና በከፍተኛ ደረጃ ከፍ አድርጎታል።

- **የደብረ ብርሃን ከተማ ልዩ ግዳጅ (ነሐሴ 1 ቀን 2015 ዓ.ም.)፦** ኮማንደር አሰግድ የፋኖን ጦር በመምራት ወደ ደብረ ብርሃን ከተማ በመግባት ከአገዛዙ "101ኛ አየር ወለድ ክፍለ ጦር" ጋር አስገራሚና ስልታዊ ውጊያ አድርጓል። በአውደ ውጊያው ላይ የጠላት ታላላቅ ምሽጎች የተሰበሩ ሲሆን፣ አብዛኛው የከተማዋ ክፍል ከጠላት ነፃ ሆኗል። የጠላት ከፍተኛ መኮንኖችና በርካታ ሰራዊት የተደመሰሱበት ሲሆን፣ ከፋኖ ሰራዊት በኩል 12 አርበኞች ሲሰዉ፣ 12 ቀላልና ከባድ ቁስለኛ መሆናቸው በታሪክ መዛግብት ተመዝግቧል።

- **የማጀቴ ስታዲየም ካምፕ የማጥቃት ጀብዱ (ነሐሴ 28 ቀን 2015 ዓ.ም.)፦** በማጀቴ ከተማ ስታዲየም መሽጎ በነበረው የጠላት ኃይል ላይ ከለሊቱ 11፡00 ሰዓት ጀምሮ መጠነ ሰፊ ጥቃት በመክፈት አብዛኛው የጠላት ኃይል እንዲደመሰስ ተደረገ። በዚህ አውደ ውጊያ በክፉኛ የተመታውና የተበሳጨው "ኮሎኔል ድባቤ" የተባለው የጠላት ጦር መሪ የደረሰበትን ኪሳራ ለመበቀል፣ በማጀቴ ከተማ ውስጥ ከ30 በላይ ንጹሐን ዜጎችን (ሴቶች፣ ሕፃናትና አረጋውያንን) በጭካኔ ረሸነ። ይህም ድርጊት ሕዝቡ ከአገዛዙ ጋር ያለውን ግንኙነት ፈጽሞ እንዲበጥስና "ፋኖ አሳ ነው፣ ሕዝብ ደግሞ ባሕር ነው" የሚለውን መርህ በተግባር በማረጋገጥ ለፋኖ ሙሉ ደጀን እንዲሆን አድርጓል።

- **የመስቀል በር የመጀመሪያው ታላቅ ደፈጣ (ሕዳር 16 ቀን 2016 ዓ.ም.)፦** በኤፍራታና ግድም ወረዳ፣ መስቀል በር ቀበሌ ልዩ ስሙ "አርብ ገበያ" በተባለ ስፍራ፣ ከአጣዬ ተነስቶ ወደ መንዝ ጌራ (መሃል ሜዳ) ሊወጣ የነበረውን የጠላት ኃይል በደፈጣ ውጊያ በሦስት አቅጣጫ በመቁረጥ ታላቅ ድል ተመዝግቧል። አንድ ኮሎኔልና አምስት ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች የነበሩባት ፒካፕ መኪናን ጨምሮ የጠላት ኃይል ሙሉ በሙሉ ወድሟል። አገዛዙ የደረሰበትን ክፉ ምት ለመደበቅ ሄሊኮፕተሮችን በማሰማራት የታዋቂ መኮንኖቹን አፅም ለመውሰድ ተገዷል።

- **የቆሪ ሜዳ ድል (መጋቢት 22 ቀን 2016 ዓ.ም.)፦** በኤፍራታና ግድም በቆሪ ሜዳ ላይ መሽጎ ከነበረው የጠላት ኃይል ጋር እልህ አስጨራሽ አውደ ውጊያ ተካሂዷል። የአፄ ይኩኖ አምላክ ክፍለ ጦር "ፕሮፌሰር አስራት ብርጌድ" በጠላት ላይ ከባድ ክንዱን በማሳረፉ ውጊያው በፋኖ የበላይነት ተጠናቆ፣ ጠላት ቆሪ ሜዳን ጥሎ ወደ ጨፋ ሮቢትና አጣዬ ከተማ ፈርጥጧል።

- **የክፍለ ጦሩ ታላቅ ምርቃት (ግንቦት 25 ቀን 2016 ዓ.ም.)፦** ለመጀመሪያ ጊዜ በሚባል መልኩ አፄ ይኩኖ አምላክ ክፍለ ጦር ከ2,000 በላይ የሚሆነውን የፋኖ ሰራዊት በማጀቴ ከተማ ታላቅ ወታደራዊ ትርኢትና ሰልፍ በማካሄድ ለጠላት መርዶ፣ ለወገን ደግሞ ታላቅ አለኝታነቱን አሳይቷል። ጨፋሮቢት ከትሞ የነበረው የጠላት ኃይል ሰልፉን ለመበተን ከባድ መሳሪያዎችን ቢተኩስም፣ የውትድርና ሥነ-ሥርዓቱ ያለምንም መስተጓጎል ተጠናቋል። ኮማንደር አሰግድም በሰራዊቱ ፊት በመቅረብ ታሪካዊ ንግግርና ወታደራዊ ስምሪት ሰጥቷል።

- **የመሃል ሜዳ ውጊያ (ሰኔ 9 ቀን 2016 ዓ.ም.)፦** ከታላቅ ወታደራዊ ተሃድሶ ማግስት፣ ከስድስት ሻለቃ በተውጣጣ ኃይል በመንዝ ጌራ ወረዳ፣ መሃል ሜዳ ከተማ ላይ ከትሞ በነበረው የጠላት ኃይል ላይ የከበባ ጥቃት ተፈጸመ። በውጊያው ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችን ጨምሮ በርካታ ሰራዊት የተደመሰሰ ሲሆን፣ ጠላት ከዘመሮና ከሞላሌ ከተማ ተጨማሪ ኃይል በማንቀሳቀስ ነበር በፋኖ ቁጥጥር ስር የነበረችውን መሃል ሜዳን

ለመውሰድ የሞከረው። የጠላት ጦር በከባድ ሁኔታ በማለቁ የተነሳ ትምህርት ቤቶች ሳይቀሩ የቁስለኛ መታከሚያ መሆናቸውን ከከተማው የደረሰው የሕዝባዊ ደህንነት መረጃ ያረጋግጣል።

**የጦር ስልትና መለያ ባህሪያት**

ኮማንደር አሰግድ በጠላት ላይ ድንገተኛ፣ ፈጣንና ማጥቃት ላይ ያተኮረ የጦር ስልትን በመጠቀም የሚታወቅ ስትራቴጂስት ነው። ዋነኛ መለያዎቹ የሚከተሉት ነበሩ።

- **የማሳሳት ታክቲክ፦** ጠላት የፋኖን አቅጣጫ እንዳያውቅ የማሳሳት ስራዎችን ይሰራል። ወደ ጠላት የሚሄድ አስመስሎ ሳይታሰብ አቅጣጫ በመቀየር ጠላት ግራ እንዲጋባና በባዶ ሜዳ ላይ እርስ በእርሱ በከባድ መሳሪያ እንዲጨራረስ ያደርግ የነበረ ታላቅ መሪ እንደነበር አርበኛ ሲራክ ሹመቴ ይናገራል።
- **የመልክዓ-ምድር እና አምባ አጠቃቀም፦** የተፈጥሮ ምሽጎችን፣ ተራራዎችንና አምባዎችን የማንበብና ለጦርነት ስልት የመጠቀም አቅሙ እጅግ ላቀ ያለ እንደነበር አርበኛ ሃምሳ አለቃ እንግዳ አዘነ ይመሰክራል።
- **ድንገተኛ ከበባ እና ቆረጣ፦** ጠላት ባልጠበቀበት ሰዓትና ቦታ በመቅደም፣ ወታደራዊ መስመር ውስጥ በመግባትና የጠላትን የኋላ ደጀን በመቁረጥ ከአንድም ሁለት ሦስት ጊዜ በጠላት ላይ ከባድ ኪሳራ ያደረሰ የጦር ጠቢብ ነበር።
- **የሕዝብ ደጀንነትና የስለላ መረብ፦** በአብዛኛው ወጣት ከመወደዱም በላይ እንደ አባት ይታይ ስለነበረ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ጠንካራ መረጃ የሚያቀብልና የጠላትን የስለላ መረብ የሚያፈርስ ኃይል እንደነበረው አርበኛ ተስፋዬ አስፋው ይናገራል።
- **አርአያነት፦** ከአስደናቂ የጦር ስልቶቹ በተጨማሪ ለአባላቱ ያሳየው የነበረው ፍቅር፣ እኩል የመራብና የመታረዝ አርአያነት ሰራዊቱ እንደ አባት እንዲወደውና እንዲያከብረው አድርጎታል። በእድሜ ከእሱ የሚበልጡትም ሆነ እኩዮቹ "ጋሼ" ብለው ይጠሩት የነበረ ሲሆን፣ ይህ አጠራር በአማራ ባህል ትልቅ ማኅበራዊ ቅቡልነትና ተፅዕኖ ላለው ሰው የሚሰጥ የክብር መጠሪያ ነው።

**5. ያጋጠሟቸው ፈተናዎች እና ታሪካዊ ውሳኔዎች**

**የዱር ሕይወት እና የጠላት ሴራ፡** ኮማንደር አሰግድ መኮንን በትግል ዘመኑ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ፈተናዎች አልፏል። በአገዛዙ ኃይሎች በተደጋጋሚ ከተደገሱለት የስውር ግድያ ሙከራዎች በአምላክ ጥበቃ የተረፈ ሲሆን፣ በዱር በገደልና በጫካ ውስጥ በሚደረገው ተጋድሎ የፋኖ ሰራዊት በቀን አንድ ጊዜ ብቻ በሚመገብበት አስቸጋሪ ወቅት እርሱም አብሮ በመራብ፣ በመታረዝ፣ በዝናብና በብርድ በመቆራመድ የጽናት ተምሳሌት ሆኖ አልፏል። ለፋኖ ሰራዊቱ ያወርደው በነበረው ጥብቅ ድሲፕሊን የተነሳ "ፋኖነት እንደ ጋሼ ካልሆነ ይቅር" እስከመባል ደርሶ በሌሎች አካባቢዎችም እንደ አርአያነት የሚጠቀስ ወጥ የፋኖ መመሪያና ሥርዓት መስርቷል።

**የእርስ በእርስ ግጭት እና ታሪካዊ ውሳኔ፡** ኮማንደር አሰግድ፣ የእስክንድር ነጋን ከመዐሕድ ጀምሮ ያለውን ፖለቲካዊ አመለካከትና አካሄድ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። እስክንድር ነጋ በአማራ ሕዝብ የብሔርተኝነት ኡደት ውስጥ የመጀመሪያው መዐሕድ እና ሁለተኛውን ትውልድ አብን ያሉትን ፍሬ እንዳያፈሩ ካደረጉት የ"ኢትዮጵያኒስት ግሩፕ" ሐሳብ አራማጆች አንዱ እንደሆነና አሁንም በፋኖ ትግል ውስጥ ሰርጎ መግባት ትግሉን እንደሚያጠልፈው ፅኑ እምነት ነበረው። ይህንን አቋሙን የተረዳው እስክንድር ነጋ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ዕዝ ውስጥ የራሱን ተልዕኮ የሚሸከሙ ሰዎችን በመያዝ፣ በኮማንደር አሰግድ ላይ "ትግሬ ነው" እስከማለት የደረሰ የፖለቲካ ሴራና ስም ማጥፋት አካሄደ። ይህ የፖለቲካ ሴራ በማደጉ፣ በሸዋ ይንቀሳቀሱ በነበሩ ሁለት የፋኖ አደረጃጀቶች (በኮማንደር አሰግድ በሚመራው "የአማራ ፋኖ በሸዋ" እና "የአማራ ፋኖ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ዕዝ") መካከል ከባድ ደም አፋሳሽ ጦርነት እንዲካሄድ በመደረጉ፣ ሰኔ 23 ቀን 2016 ዓ.ም በኮማንደር አሰግድ ይዞታ በነበረው በአፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር ላይ ወረራ ተፈጸመ።

በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ኮማንደር አሰግድ የአማራ ደም በከንቱ እርስ በእርሱ እንዳይፈስ በማሰብ የሚከተለውን ታሪካዊና አስተዋይ ውሳኔ አስተላለፈ።

**"እኔ ለጠላት እንጂ እርስ በርስ የአማራን ሕዝብ የሕልውና ትግል ለመመከት የወጣ የአማራ ወጣት ላይ ልተኩሰው የገዛሁት ጥይት የለም።"** በማለት የነበረበትን ቀጠና ለቆ ወጣ። ሰኔ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከአካባቢው ለቆ ከወጣ በኋላም በድጋሚ በውስጥ ኃይሎች የእርስ በእርስ ጥቃት ተፈጸመበት።

**በጠላት እጅ መውደቅ፡** ከእርስ በእርስ ወረራዎች በመሸሽና ጦሩን ይዞ ቀጠናውን ለቆ በመንቀሳቀስ ላይ ሳለ፣ በጥናትና በክትትል ውስጥ በነበረው የጠላት የደህንነት መረብ ውስጥ ሊገባ ችሏል። በዚህም ሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም በኮምቦልቻ ከተማ በጠላት እጅ ወደቀ። "ጋሼ ተያዘ" የሚለው መርዶ በመላው ሰራዊትና ደጋፊ ዘንድ ታላቅ ሐዘንን ፈጥሯል። አገዛዙ "እጅ ሰጠኝ" የሚል የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ቢከፍትም፣ የቁርጥ ቀን አርበኛነቱን የሚያውቅ ሕዝብ አልተቀበለውም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አገዛዙ አንድ ቀን ብቻ በቴሌቪዥን ከማሳየቱ በቀር፣ እስካሁን ድረስ በሕይወት ይኑር ወይም ይሙት በግልጽ የታወቀ ነገር የለም።

## 6. የቤተሰብ ሕይወት እና የታሪክ አሻራ

- **የቤተሰብ ሕይወት፡-** ኮማንደር አሰግድ መኮንን የሦስት ልጆች (የአንድ ሴት እና የሁለት ወንድ ልጆች) አባት እና አፍቃሪ፣ አርአያ የሚሆን የቤተሰብ መሪ ነበር።
- **የታሪክ አሻራ እና ውርስ፡-** በአማራ ሕዝብ እና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በብዕርም በሰይፍም የተዋጋ ታላቅ ሰው ነው። ለንባብ ካበቃቸው ከ15 በላይ መጻሕፍት ባሻገር፣ ሳይታተሙና ለሕዝብ ሳይበቁ በእጅ ጽሑፍ ደረጃ ያሉ በርካታ ያልወጡ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች አሉት። የእርሱ ትልቁ የታሪክ አሻራ ግን የአማራን ሕዝብ የማንነት ጥያቄ በተደራጀ መንገድ የመራበት፣ የፋኖን መዋቅር ተቋማዊና ስልታዊ ያደረገበት እና "ሆዳም ትውልድ ሀገርም ታሪክ የለውም" የሚለውን መርሆ በተግባር ያሳየበት የነፃነት ተጋድሎው ነው።

## ፕሮፋይሉን ለማዘጋጀት የተወሰዱ ታማኝ ምንጮች

1. **አርበኛ ሃምሳ አለቃ እንግዳ አዘን፡-** የአፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር ምክትል አዛዥ የነበረ።
2. **አርበኛ ተስፋዬ አስፋው፡-** የኮማንደር አሰግድ መኮንን የቅርብ ፕሮቶኮል የነበረ እና በአሁኑ ጊዜ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኮር ሀብት አሰባሳቢ።
3. **አርበኛ ሲራክ ሹመቴ፡-** የኮማንደር አሰግድ መኮንን አጃቢ የነበረ፣ አሁን የአሳምነው ዕዝ ባህል እና መዝናኛ ክፍል ኃላፊ።
4. **አርበኛ ኢ/ር ደሳለኝ ሲያስብሸዋ፡-** በጊዜው የኮማንደር አሰግድ ምክትል የነበረ እና በአሁኑ ሰአት የአፋብን ሸዋ ጠቅላይ ግዛት አሳምነው ዕዝ ዋና ሰብሳቢ የሆነ።
5. **አርበኛ ጠበቃ እና የሕግ መምህር ተስፋዬ ገስጥ፡-** በጊዜው የአፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር ሕግ ክፍል ኃላፊ የነበረ እና በአሁኑ ሰአት የአፋብን የሕግ እና ስነ-ስርዓት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ
6. **አርበኛ አሸናፊ ምንዳ፡-** በጊዜው የአፄ ይኩኖ ዓምላክ ክፍለ ጦር የፖለቲካ ክፍል ኃላፊ እና የዕዙ የሰው ኃይል መምሪያ ኃላፊ የነበረ አሁን ላይ የአፋብን ምክትል ለፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ ናቸው።